# የአድራሻ ሚስጥራዊነት ፕሮግራም

የዲስትሪክቱ **የአድራሻ ሚስጥራዊነት ፕሮግራም** (ACP)፣ በተጠቂ አገልግሎቶች እና ፍትህ አሰጣት ቢሮ (OVSJG) የሚተዳደር፣ የጉዳት ስጋት ያለባቸው ሰዎች ደህንና ሆነው እንዲቆዩ ያግዛል፣ የጎዳና አድራሻቸውን ከህዝብ መዝገቦች በመደበቅ። የACP አገልግሎቶች በሰፊዎ የግለሰብ ደህንነት እቅድ ውስጥ እንደ አንድ መሳሪያ ይታሰባሉ።

ይህ ነጻ ፕሮግራም የሚከተሉትን ለተሳታፊዎች ያቀርባል፥

- ህጋዊ የሆነ የመተኪያ አድራሻ **ቤታቸውን፣ ስራቸውን፣ ወይም የትምህርት ቤት አድራሻቸውን ለመጠበቅ**
- ሚስጥራዊ የሆነ **የፖስታ-መላኪያ** አገልግሎት።

## ለማን ነው የሚሰጠው?

በሚከተሉት ሁኔታዎች ውስጥ ለACP ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ፥

(1) ለደህንነትዎ ከሰጉ፤

(2) ባሁን ጊዜ (ወይም በቅርብ ጊዜ ውስጥ) የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ፤ *እና*

(3)
- የቤት ውስጥ ጥቃት፣ ጾታዊ ጥቃት፣ መከታተል፣ ወይም የሰው ዝውውር ጥቃት አጋጥሞት ከሆነ፤
- ዋና ዓላማቸው ከላይ የተጠቀሱ ጥቃቶች የደረሱባቸው ተጠቂዎችን ማገልገል የሆነ ድርጅት ውስጥ ተቀጥረው ከሆነ፤ *ወይም*
- የስነ-ተዋልዶ ጤና እንክብካቤ ላይ ትኩረት የሚያደርግ ድርጅት ውስጥ ተቀጥረው ከሆነ።

በተጨማሪም አመልካቾች የሚከተሉትን እንዲያደርጉ ይፈለጋሉ፥ ባለፉት 60 ቀናት ውስጥ የተዘዋወሩ መሆን፣ በሚቀጥሉት 30 ቀናት ውስጥ ለመዛወር እያቀዱ መሆን፣ ወይም ያሁኑ አድራሻቸው በኦንላይን ወይም በህዝብ መዝገቦች አማካኝነት በቀላሉ እንዳይገኙ ለመረጋገጥ በቂ እርምጃዎችን የወሰዱ መሆን። ሁለቱም አዋቂዎች እና ልጆች ሊያመለክቱ ይችላሉ።

## ማመልከቻው እንዴት ይፈጸማል

**የማመልከቻ አጋዦች** ጥያቄዎችን ለመመለስ፣ ብቁነትን ለማረጋገጥ፣ እና ማመልከቻዎችን ለመቀበል በዲስትሪክቱ ውስጥ ያሉ በርካታ ኤጀንሲዎች ውስጥ ይገኛሉ። እንዲሁም እነሱ የመብት ክርክር አገልግሎቶችን ማቅረብ እና በግል ፍላጎቶችዎ መሰረት ሁለንተናዊ የደህንነት እቅድ ለማዘጋጀት ሊረዱዎት ይችላሉ።

ስለ ACP የበለጠ ለማወቅ ወይም ማመልከቻዎችን ለማስገባት የሚከተለው ድህረ ገጽ ላይ በተዘረዘሩ ማንኛውም ድርጅቶች ውስጥ ያሉ የማመልከቻ ረዳቶችን ያግኙ፥ ovsjg.dc.gov/acp።

## ACP እንዴት ይሰራል?

### ተተኪ አድራሻ

ብቁ የሆኑ አመልካቾች የACP **መፍቀጃ ካርድን** ከተተኪ አድራሻ ጋር ይቀበላሉ። ይህ ካርድ የእውነተኛ ቤትዎ፣ ስራዎ፣ ወይም የትምህርት ቤት አድራሻዎ ቦታ ለማንኛውም የዲሲ ኤጀንሲ መቅረብ ይችላል። የመፍቀጃ ካርዶች መጀመሪያ ለ3 ዓመታት ተቀባይነት አላቸው።

በዚህ ህጋዊ ተተኪ አድራሻ ትክክለኛ አድራሻዎ በህዝብ መዝገቦች ውስጥ የመገኘት ስጋት ሳይገባዎ ከዲሲ ኤጀንሲዎች ጋር መገናኘት ይችላሉ። በተተኪ አድራሻ የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፥

- የዲሲ መንጃ ፍቃድ ወይም መታወቂያ ካርድ ማግኘት
- ልጆችን የዲሲ የህዝብ/ቻርተር ትምህርት ቤት ውስጥ ማስመዝገብ
- መምረጥ እና ፊርማ መሰብሰብ ላይ መፈረም

የዲስትሪክት ኤጀንሲዎች ብቻ የተተኪ አድራሻዎን እንዲያከብሩ የሚጠየቁ ቢሆንም፣ እርሱን የዲሲ መንጃ ፍቃድ ወይም መታወቂያ ካርድ ላይ ማስቀመጥ በብዙ የእለት-ተእለት ሁኔታዎች ውስጥ ትክክለኛ አድራሻዎን ይጠብቃል።

### ፖስታን አስተላልፎ መላክ

የመጀመሪያ-ደረጃ፣ የተረጋገጠ፣ ወይም የተመዘገበ ፖስታ በተተኪ አድራሻዎ ሲደርስ፣ ወደ ቤት አድራሻዎ ተላልፎ ይላካል።

### ገደቦች

ተተኪ አድራሻ ትክክለኛ አድራሻዎ በሌሎች መንግስታዊ-ያልሆኑ ኤጀንሲዎች እንደማይጠየቅ ዋስትና አይሆንም። ትክክለኛ አድራሻዎ አሁንም ለተወሰኑ ተግባራት ይፈለጋል፣ የሚከተሉትን ጨምሮ፥

- ቤት ወይም ንብረት መግዛት። (አድራሻው በተያያዙ የህዝብ ዝርዝሮች ውስጥ ሊታይ እንደሚችል ያስታውሱ።)
- በቤትዎ ላይ ለብድር መስመር ለማመልከት።
- ለቤትዎ መገልገያዎችን ለማዋቀር።

በተጨማሪ፣ ACP ትርኪ ምርኪ ፖስታዎችን፣ እሽግ መልዕክቶችን፣ ወይም ጋዜጣዎችን አሳልፎ አይልክም፤ የመብት ተከራካሪ ወይም የማመልከቻ ረዳት ያንን ፖስታ በደህንነት ለመቀበል እንዲያቅዱ ሊረዱዎት ይችላሉ። ሌሎች ገደቦች በተጨማሪ መተግበር ይችላሉ።


**የአድራሻ ሚስጥራዊነት ፕሮግራም**

ACP@dc.gov • (202) 788-2131

Office of Victim Services and Justice Grants
441 4th St., NW, Ste 727N
Washington, DC 20001
(202) 727-0605



OVSJG Office of Victim Services and Justice Grants

WE ARE WASHINGTON DC GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA MURIEL BOWSER, MAYOR